# ፳፪. ባሕታዊ አባ ቤጂሚ

# (ABBA BEJIMI THE HERMIT)

አባ ቤጂሚ በአባ ማሲል ሀገረ ስብከት ሥር በነበረችው በፊስሀ (Fisha) ከተማ ከድሀ ክርስቲያን ቤተሰብ ተወለደ። ዐሥራ ሁለት ዓመት ሲሞላው የአባቱን በጎች መጠበቅ ጀመረ፤ የአባቱን በጎች በመጠበቅ ላይ እያለ የእግዚአብሔር መልአክ በታዳጊ ልጅ አምሳል ሆኖ ተገለጠለትና "በዚህ ምድር ላይ ያለውን ቀሪ ሕይወታችንን እነዚህን እንስሳት በመጠበቅ ፋንታ እግዚአብሔርን በማምለክ እንኖር ዘንድ ከእኔ ጋር መምጣትና አብረኸኝ መነኩሴ መሆን ትፈልጋለህ? ከሦስት ቀን በኋላ ሦስት መነኰሳት መጥተው ወደ ገዳማቸው ይወስዱኛልና አንተም ከፈለግህ መምጣት ትችላለህ" አለው። የታዳጊው የቤጂሚ ልብ እጅጉን ደስ ተሰኘች ምንኩስና የዘወትር የልቡናው መሻት ነበረና። ስለሆነም አዲሱን ባልንጀራውን "አዎ እፈልጋለሁ፤ እባክህ ውሰደኝ" አለው።

ከሦስት ቀናት በኋላ ሦስት መነኰሳት ቤጂሚ ወደሚጠብቅበት ሜዳ እየተጓዙ መጡ። መልአኩ ወደ እነርሱ ቀረብ አለና "ለዓለም የሚያበራ መብራት የሚሆነውን ይህን ብሩህ ምሰሶ ከእናንተ ጋር ብትወስዱት መልካም ነው እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠ ነውና። እርሱም በመጨረሻዎቹ ቀናት (በሥጋ ከመሞቱ በፊት) ወደዚህ ቦታ ይመለሳል፤ እግዚአብሔርም በእርሱ በኩል በዚህ ምድር ላይ ተጋድሎውን እስኪጨርስ ድረስ ብዙ ተአምራትን ያደርጋል" አላቸው።

እነርሱም ይህን ቃል የተናገራቸው የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን በመረዳት ከመነኰሳት ሽምገል ያለው መነኩሴ ወደ ታዳጊው ቅዱስ ወደ ቤጂሚ ቀረብ አለና "ከእኛ ጋር መምጣት ትፈልጋለህ? ነገር ግን





መንገዱ በጣም ረዥምና አድካሚ መሆኑን አስጠነቅቅሃለሁ" አለው። ቤጂሚም "በታላቅ ፍቅር እከተላችኋለሁ" አለው። እርሱም ከኒጥራ ተራራ (Mount Nitria) እስኪደርሱ ድረስ አብሯቸው ተጓዘ፤ በዚያም ከእነርሱ ጋር ለጥቂት ቀናት ዐረፈ። ከዚያም በሲሃት ምድረ በዳ ውስጥ ለተጨማሪ ሰባ ቀናት መጓዛቸውን ቀጠሉ።

በመንገድ ሲጓዙ መነኮሳቱ ታዳጊውን ሕፃን ቤጂሚን ስለምንኩስና ሥርዐት ና ባህል አስተማሩት፤ ትህትናን፣ ጸሎትን፣ ጾምን፣ ትጋትን፣ የእጅ ሥራን እና ቅዱሳት መጻሕፍትን ማስታወስን በምሳሌ አስተማሩት። ታዳጊው ቅዱስም በፈሪሃ እግዚአብሔር፣ በትእግስት፣ በትህትናና በመንፈሳዊነት እያደገ የሚሔድ ሆነ። ሦስቱ መነኰሳትም በቤጂሚ ጠባይና መልካም ምግባራት እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን ምሥጢራት ለመሳተፍ በነበረውን ፍቅርና ትጋት ደስ ተሰኙ። ቅዱሱ ከሦስቱ አበው መነኰሳት ጋር በታማኝነትና በክርስቲያናዊ ፍቅር ለሰባት ዓመታት ከኖረ በኋላ የምንኩስናን ልብስ አለበሱት።

ቤጂሚ ውብ እና መልከ መልካም የነበረ ሰው ነው፤ ደስ በሚል ፈገግታውና በየዋህነቱ ምክንያትም "የሰላም ልጅ" ይሉት ነበር። እርሱም ወደ ሰማያዊው መንግሥት እስኪሔዱ ድረስ ለሦስቱም አባቶች ፍጹም ታዛዥ በመሆን ለዐሥራ ዐምስት ዓመታት ኖረ። ከመኖሳት አበው ጋር በነበረባቸው ዓመታት ውስጥ አንድ ቀን ታላቅ መንፈሳዊ መሪ እንደሚሆን ትንቢት ተናግረውለት ነበር። እነርሱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ከሔዱ በኋላ ለሁለት ዓመታት በዚያ ምድረ በዳ ብቻውን ተቀመጠ፤ ስለሆነም በሲሃት ምድረ በዳ ለሃያ ዐራት ዓመታት ኖረ።

የአባ ቤጂሚ ዝናው በአገሩ ሁሉ ተሰማ፤ መነኰሳት አባቶችና በዙሪያው ባሉ አገራት ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ሊያዩትና በረከት ሊቀበሉ ወደ

እርሱ ይመጡ ነበር። እርሱም ከሰዎች ጋር በመገናኘትና እነርሱንም በመምራት ጊዜውን እያጠፋ መሆኑን ባስተዋለ ጊዜ ከንቱ ውዳሴን እና የሰዎችን ምስጋና እንዲሁም በልቡ ሊያድር የሚችለውን ክፉ የትዕቢት መንፈስ ፈራ። ስለሆነም ከዚህ ዓለም በሞት የሚለይባትን ሰዓትና የፍርድን ቀን ማሰብ ጀመረና ራሱን እንዲህ እያለ መውቀስ ጀመረ፡- "እግዚአብሔር በዚች ሌሊት ቢፈልገኝ ምን ላደርግ እችላለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ልቆም እና በሕይወቴ ለሠራኋቸው ሥራዎችስ ምን ልመልስ እችላለሁ?"

ከዚያም ተነሣና በሲሃት ምድረ በዳ ውስጥ ለሦስት ቀንና ሌሊት ተጓዘ። ለመደገፊያ ከሚመረኮዝባት የዘንባባ ዝንጣፊ በስተቀር አንዳች ነገር አልያዘም ነበር። በእነዚህ ሦስት ቀናት ውስጥ ምንም አልበላም። ከዚያም ድንገት የሚበሉትና የሚያጠቁት መስለው አጋንንት በክፉ አራዊት አምሳል ሆነው መጡበት፣ ሆኖም ግን ቅዱሱን ሊቀርቡት እንኳን አልቻሉም ነበር። ስለዚህም ቤጂሚ እንዲህ አላቸው፡- "ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ እኔን ለእናንተ አሳልፎ ከሰጣችሁ ሁላችሁም በዚህ መሆን አይገባችሁም ከመካከላችሁ አንዱ ብቻ እኔን ለመግደል ብርታቱ አለውና፣ ጌታ በእኔ ላይ ሥልጣን ካልሰጣችሁ ግን ከእኔ ወግዱ!" ይህን ካለ በኋላ በመስቀል ምልክት አማተበ፣ እነርሱም እንደ ጢስ ብንን ብለው ጠፉ።

ከዚህ ክስተት በኋላ ቅዱሱ በምድረ በዳው ውስጥ መጓዙን ቀጠለ። በመጓዝ ላይ እያለ ሲጸልይ እግዚአብሔር ከጎኑ እንደሆነና እየረዳው መሆኑ ስለተሰማው ደስ አለው። በሲሃት በረሓ ውስጥ ለተጨማሪ ሁለት ቀናት ከተጓዘ በኋላ ንጹሕ ውኃና ብዙ የዘንባባ ዛፎች ያሉባት አንዲት ትንሽ ሸለቆ አገኘ። ከውኃው ብዙ እንስሳት ሲጠጡ ሲያይ እጅግ ደስ ተሰኘ።





አባ ቤጂሚ ከአንድ ትልቅ ተራራ አጠገብ የምትገኝ አንዲት ዋሻ አስኪያገኝ ድረስ ሃያ ማይሎችን ተጓዘ። ይች በኣትም ለቀጣዮቹ ሃያ ዐራት ዓመታት በጥብቅ የብሕትውና ሥርዐት ፣ ከልብ በመነጨ ጸሎት እና በፍጹም ትህትና የኖረባት ቤቱ ሆነችለት፣ ሁል ጊዜም "ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፣ ከእኔም ተማሩ፣ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፣ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ" /ማቴ 11÷29/ ያለውን የጌታን ትእዛዝ ያስታውስ ነበር።

በዚች በኣት ውስጥ መኖር በጀመረ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት ውስጥ በስድስት ቀን አንድ ጊዜ ብቻ ይበላና ይጠጣ ነበር። የቴምር ፍሬ ይበላ ነበር፣ ውኃም ከንጹሑ ምንጭ ይጠጣ ነበር። በበኣቱ ውስጥ ምግብም ይሁን ውኃ አስቀምጦ አያውቅም።

በየቀኑ ሃምሳ መዝሙራትን ከመዝሙረ ዳዊት ይጸልይ ነበር፣ ከሙሴና ከነቢያት መጽሐፍም ያነብብ ነበር። ጠዋት ዐራት መቶ ስግደት ይሰግዳል፣ ሌሊት ደግሞ ይንበረከክና በድጋሜ ሃምሳ መዝሙራትን ከመዝሙረ ዳዊት ይጸልያል፣ ከምስጋናና ከጸሎት ጋር ብዙ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን፣ እንዲሁም ከወንጌላትና ከመልእክታት ያነብብ ነበር።

ከሦስት ዓመታት በኋላ ልብሶቹ አለቁ፣ በዚህ ጊዜ የመጀመሪያውን ባሕታዊ አባ ጳውሊን አስታወሰ፣ ስለሆነም ለራሱ ከዘንባባ ልብስ አዘጋጀ። በእነዚህ ሦስት ዓመታት ጽኑ መንፈሳዊ ተጋድሎን ተጋደለ፣ ስለዚህም የእግዚአብሔር መልአክ አውሬ በሚያድ'ን አዳ'ኝ አምሳል ተገለጠለትና በአንድ ወቅት መልአኩ ለነቢዩ ኤልያስ እንደሰጠው ለአባ ቤጂሚ ሰማያዊ መና ሰጠው።

በምድረ በዳ ለሃያ ዐራት ዓመታት ከኖረ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ሊቀ መላእክት ሚካኤል እና ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ወደ ቤጂሚ መጡ፣ ምድረ በዳውም በብርሃን ጎርፍ ተጥለቀለቀ። ጌታችንም ቅዱሱን "የመረጥሁት ወዳጄ ሆይ፣ ሰላም ለአንተ ይሁን! ለእኔ ስላለህ ፍቅር እና ለእኔ ስትል ስለተቀበልኸው መከራ ምክንያት በስምህ ቤተ ክርስቲያን ይታነጽልሃል። ..." አለው። ከዚያም ቤጂሚን ባረከውና "ተነሣና ወደ ትውልድ ከተማህ ሐኤድ በዚያ በስምህ ብዙ ገዢ ተአምራትን አደርጋለሁና፣ ጣዖት አምላኪዎችም ወደ እውነተኛዋ ሃይማኖት ይመለሳሉ። በምድር ላይ ያለውን ተጋድሎህን ከመፈጸምህ እና ከእኔ ጋር በሰማዩ መንግሥቴ ለዘለዓለም ለመኖር ከመምጣትህ በፊት ለዐሥር ዓመታት ትኖራለህ" አለው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአርሱ ከመለየቱ በፊት ለአባ ቤጂሚ ሰላሙንና በረከቱን ሰጠው። ከዚያም ሊቀ መላእክት ሚካኤል ቅዱሱን በደመና ላይ አስቀመጠውና ደመናውም ቅዱሱን ተሸክሞ ከትውልድ ከተማው ሦስት ማይሎች ርቀ ከሚገኝ ታላቅ ተራራ ላይ አደረሰው። በዚያም ቤጂሚ አንዲት ትንሽ በኣት ሠርቶ ጥብቅ በበሆነ የብሕትውና ሕይወት እና በፍጹም አምልኮ ኖረ። አርሱ ለሚያዩት ሁሉ የጽድቅ ምሳሌ ነበር።

ከጥቂት ቀናት በኋላ የጌታ መልአክ ተሸክሞ ፍልስጥኤም ወደምትኘ ፋራን (Pharan) ወደምትባል አውራጃ ወሰደው በብዙ ከሃዲያን ጠፍታ ነበርና፣ ሆኖም ግን በአባ ቤጂሚ መንፈሳዊ ትምህርት ብርታት እና በእርሱ ላይ ባደረው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ምክንያት ሁሉንም ከሃዲያን ተቋቋማቸው። እግዚአብሔርም ገዢ ተአምራት የማድረግ፣ ህሙማንን የመፈወስ እና አጋንንትን የማስወጣት ጸጋ ሰጠው።

አባ ቤጂሚ በፋራን አውራጃ እየጸለየና የጠፉ በጎችን ወደ መጋው ለመመለስ እየተጋደለ ዐምስት ዓመታትን አሳለፈ። እግዚአብሔር ይህን ተግባሩን ዳር ያደርሰው ዘንድ ከረዳው በኋላ መልአክ ተሸክሞ





ከትውልድ ከተማው አጠገብ ወደምትገኘው በኣቱ መለሰው። በዚያም ብዙዎችን ወደ አማናዊቷ ሃይማኖት እንዲመለሱ እያበረታታ እና ህሙማንን እየፈወሰ ለዐምስት ዓመታት ኖረ። በዚህ ምክንያት ዝናው በአገሩ ሁሉ ተሰማ።

በአንድ ወቅት አበምኔት አባ ሺኖዳ በአንዱ ሌሊት ራእይ እንዳየ ተነግሮ ነበር፡- ዐይኖቹን ወደ ሰማይ አትንቶ ሲመለከት በብርሃን አምድ ላይ በነበረ አንድ ዕፁብ ድንቅ ዙፋን ላይ ከሚያንፀባርቁ አልማዞች የተሠራ አክሊል ተቀምጦ አየ። እርሱም ከመላእክት አንዱን "ይህ አክሊል የማን ነው?" ብሎ በጠየቀው ጊዜ መልአኩም "ይህማ በማሲል ሀገረ ስብከት ሥር የምትገኘው የፊስሀው ቅዱስ አባት የባሕታዊ አባ ቤጂሚ ነው" አለው። ከዚህ መገለጥ በኋላ አባ ሺኖዳ ቅዱሱን ለማየት ጓጓ፣ ስለዚህም እስኪያገኘው ድረስ ዝም ብሎ ወደ ምድረ በዳ ተጓዘ። በተገናኙ ጊዜ የተባረከው ቅዱስ አባ ቤጂሚም አባ ሺኖዳ ማን እንደሆነ በመንፈስ አወቀ፣ ስለሆነም ተቃቅፈው ተሳሳሙ። ሙሉ ሌሊቱን በእንድነት ሲጸልዩና ሲያመሰግኑ ከዚያ በኋላም ስለ እግዚአብሔር ታላላቅ ተአምራትና ድንቆች ሲያወሩ አደሩ። አባ ሺኖዳ ወደ ገዳሙ ከመመለሱ በፊት የተወሰኑ ቀናትን ከቅዱሱ ጋር ቆዩ።

እግዚአብሔር ለአባ ቤጂሚ ከዚህ ዓለም በሞት የሚለይበትን ሰዓት ገለጠለት፣ ስለሆነም ደቀ መዝሙሩን ጠራውና ነፍሱ ከሥጋው ስትለይ ሊታወቅ የሚችልበትን ምልክት ሰጠው።

ቅዱሱ አባት አባ ቤጂሚ በክብር የትኩሳት ህመም ሊያገ ታጎሣሥ አንድ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ነበር፣ ሆኖም ግን በህመሙ ጊዜ ሊነሽጉት በመጡ በብዙ ቅዱሳን ተጽናና። በተባረከው በታጎሣሥ ወር በአስራ አንደኛው ቀን ቅዱሱ አባት አባ ቤጂሚ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ፣ ሠራዊተ መላእክትም ነፍሱን ተሸክመው በፍጹም ልቡ ወደሚወደው

ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወሰዷት። አባ ቤጂሚ ነፍሱ ከሥጋው ስትለይ ሰባ ዓመቱ ነበር።

በተወለደባት በፊስሀ ከተማ ዐሥራ ሁለት ዓመት፣ በሊሃት በረሓ ከገዳም አባቶች ጋር ሰባት ዓመት፣ የምንኩስና ልብስን ሰዉሶ በሊሃት በረሓ አሥራ ሰባት ዓመት፣ በምድረ በዳው ውስጥ እየተዘዋወረ ሃያ ዐራት ዓመት፣ በፋራን ዐምስት ዓመት እና ከትውልድ ከተማው አጠገበ በምትገኝ በኣት ዐምስት ዓመት ኖረ።

በታላቁ በአባ መቃርዮስ ገዳም ውስጥ "በባሕታውያን አባቶች ስም የተሠራ ቤተ ክርስቲያን አለ። በዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተቀረዘው ባሕታዊ አባት የአባ ቤጂሚ ስዕል አለ። ቤተ ክርስቲያናችን የቅዳሴ አባ ቤጂሚን በዓል በየአመቱ ታኅሣሥ 11 ታከብራለች።

**የቅዱሱ አባት የአባ ቤጂሚ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን።**






@HIWOTEMENEKOSAT